Public Health
Seattle & King County

# አምስተኛ በሽታ

**ውድ ወላጅ ወይም አሳዳጊ፣**

**ይህ የመረጃ ወረቀት እየተሰጠዎት ያለው፦**

**☐ እርስዎ ወይም ልጅዎ ለአምስተኛው በሽታ ተጋልጠው ሊሆን ስለሚችል ነው።**

**☐ ለመረጃ አገልግሎት አላማዎች ብቻ የሚውል።**

---

## ስለ አምስተኛው በሽታ አጠቃላይ መረጃ

### አምስተኛው በሽታ ምንድን ነው?

- አምስተኛው በሽታ ፓርቮ ቫይረስ B19 በተባለ ቫይረስ የሚመጣ መካከለኛ በሽታ ነው።
- በተጨማሪም “slapped cheek disease (በጥፊ የተመታ ጉንጭ በሽታ)” ወይም Erythema Infectiosum (ኢሪተማ ኢንፌክሽሰም፣ EI) በመባል ይታወቃል።
- በጣም የተለመደው በክረምት መጨረሻ፣ በጸደይ እና በበጋ ወራት መጀመሪያ ላይ ነው።

### ማን ሊይዘው ይችላል?

- ማንኛውም ሰው በአምስተኛው በሽታ ሊያዝ ይችላል።
- በልጆች ላይ በጣም የተለመደ ነው።
- በአምስተኛው በሽታ የሚያዙ አንዳንድ ሰዎች በጣም ለመታመም ወይም ለህክምና ችግሮች የመጋለጥ እድላቸው ከፍተኛ ነው፣ እነዚህም የሚከተሉትን ያካትታሉ፦
  - ሲክል ሴል በሽታ ያለባቸው።
  - ስር የሰደደ የደም ማነስ ያለባቸው።
  - የተዳከመ በሽታ የመቋቋም ስርዐት ያለባቸው።
  - ነፍሰጡር የሆኑ።
- **በከፍተኛ ሁኔታ ተጋላጭ በሆኑ ቡድን ውስጥ ያሉ ሰዎች (ከላይ ያለውን ይመልከቱ) ለአምስተኛው በሽታ እንደተጋለጡ ወይም እንዳለባቸው ካሰቡ የጤና እንክብካቤ አቅራቢያቸውን ማነጋገር አለባቸው።**

### ምልክቶቹ ምንድን ናቸው?

- ትኩሳት (American Academy of Pediatrics (የአሜሪካ የህጻናት ህክምና አካዳሚ) ትኩሳትን እንደ 100.4°F [38°C] ወይም ከዚያ በላይ የሙቀት መጠን ይገልጸዋል)
- የድካም ስሜት
- የአፍንጫ ፈሳሽ
- ራስ ምታት
- የጡንቻ ህመም
- ሌሎች ምልክቶች ከታዩ በኋላ ሽፍታ ከቀናት እስከ ሳምንት ባለው ይታያል። በጉንጮች ላይ ያለው ሽፍታ ደማቅ ቀይ ሲሆን፣ “በጥፊ የተመቱ” እንዲመስሉ ያደርጋቸዋል።
- ከዚያም ሽፍታው ወደ ደረት፣ ሆድ፣ እጆች እና እግሮች ይሰራጫል፣ እንዲሁም በቆዳ ላይ ወደ ቀይ ምልክቶች ይለወጣል (ብዙውን ጊዜ ቀለል ያለ ቀለም አለው)።

- የምልክቶቹ መሃል መጽዳት ሲጀምሩ፣ ሽፍታው ዳንቴል የሚመስል መልክ ይኖረዋል።
- ሽፍታው ከጠፋ በኋላ፣ ለብዙ ሳምንታት ለሙቀት በሚጋለጥበት ጊዜ ሊመለስ ይችላል።
- በአምስተኛ በሽታ የሚያዙ አዋቂዎች በልጆች ላይ እንደሚታየው ተመሳሳይ ሽፍታ፣ እንዲሁም የመገጣጠሚያ ህመም እና እብጠት ሊኖርባቸው ይችላል።
- የተለመደ ባይሆንም፣ ሌሎች ምልክቶች ማሳከክ፣ ሳል፣ ተቅማጥ፣ ማስታወክ፣ የአፍንጫ ፈሳሽ ወይም የመገጣጠሚያ ህመምን ሊያካትቱ ይችላሉ።
- አምስተኛው በሽታ ያለባቸው ብዙ ሰዎች ምልክቶች አይኖራቸውም።

### አምስተኛው በሽታ እንዴት ይተላለፋል?

- አምስተኛውን በሽታ የሚያመጣው ቫይረስ ከሳል፣ ከማስነጠስ፣ ከለሃጭ እና ከአፍንጫ ፈሳሽ በሚወጡ ጠብታዎች ውስጥ ይገኛል።
- አምስተኛው በሽታ ያለበት ሰው ሲያስል ወይም ሲያስነጥስ እና ሌላው ሰው ጠብታዎቹን ወደ ውስጥ ሲተነፍስ ቫይረሱ ሊሰራጭ ይችላል።
- እንዲሁም በሚከተሉት ሊሰራጭ ይችላል፦
  - ቫይረሱ ያለበትን ነገር ወይም ንጣፍ መንካት ከዚያም አፍን፣ አይንን ወይም አፍንጫን መንካት።
  - አምስተኛው በሽታ ካለበት ሰው ጋር እቃዎችን ወይም ኩባያዎችን መጋራት።
- አምስተኛው በሽታ 'ጉንፋን ብቻ' በሚመስልበት በበሽታው መጀመሪያ ላይ በቀላሉ ከሰው ወደ ሰው ይተላለፋል። ሽፍታው ከታየ በኋላ፣ አንድ ሰው ቫይረሱን ማሰራጨት አይችልም።
- ቫይረሱ የሚያጠቃው ሰዎችን ብቻ ነው። የእንስሳት ፓርቮቫይረሶች የተለዩ ናቸው፣ ስለዚህ ድመቶች እና ውሾች አምስተኛውን በሽታ ማሰራጨት አይችሉም።

---

## ልጄ አምስተኛ በሽታ እንዳለበት እንዴት አውቃለሁ?

- አንድ የጤና እንክብካቤ አቅራቢ በተለምዶ በግለሰቡ ላይ ባሉት ምልክቶች ላይ በመመርኮዝ አምስተኛውን በሽታ መመርመር ይችላል።
- በአንዳንድ አጋጣሚዎች፣ የጤና እንክብካቤ አቅራቢ ለቫይረሱ ጸረ እንግዳ አካላትን ለመመርመር የደም ምርመራን ሊያዝ ይችላል።

**ተጨማሪ ጥያቄዎች ካሉዎት ወይም ልጅዎ አምስተኛው በሽታ እንዳለበት የሚያሳስብዎ ከሆነ፣ የጤና እንክብካቤ አቅራቢዎን ያነጋግሩ። ይህ የመረጃ ሉህ አጠቃላይ መረጃ ብቻ ይሰጣል።**

---

## ልጄ አምስተኛው በሽታ ቢይዘውስ?

**ልጅዎ አምስተኛ በሽታ ካለበት ወዲያውኑ ለልጅዎ እንክብካቤ አቅራቢ ወይም ቅድመ ትምህርት ቤት ያሳውቁ።**

### እንዴት ይታከማል?

- አብዛኛውን ጊዜ አምስተኛው በሽታ በራሱ የሚድን መካከለኛ በሽታ ነው።
- ህጻናት ምቾት እንዲሰማቸው ያድርጉ፣ እንዲያርፉ ይፍቀዱላቸው፣ ድርቀትን ለመከላከል ብዙ ፈሳሽ መጠጣታቸውን ያረጋግጡ እንዲሁም በተደጋጋሚ ይመልከቷቸው።

- 100.4°F (38°C) ወይም ከዚያ በላይ የሆነ ትኩሳት ያላቸው የ3 ወር ወይም ከዚያ በታች የሆኑ ጨቅላ ህጻናት በጤና እንክብካቤ አቅራቢያቸው መታየት አለባቸው።
- ስለ ልጅዎ የበሽታ ምልክቶች የሚያሳስብዎት ነገር ካለ ከልጅዎ የጤና እንክብካቤ አቅራቢ ጋር ይነጋገሩ። **ልጅዎ የድርቀት ምልክቶች እያሳየ ከሆነ (ትንሽ እርጥበት ያላቸው ዳይፐሮች ወይም ከወትሮው ያነሰ ሽንት፣ ከመደበኛው የበለጠ ድካም፣ ማዞር፣ ደረቅ ምላስ ወይም ከንፈር፣ ትንሽ እንባ) ወዲያውኑ በጤና እንክብካቤ አቅራቢው መታየት አለበት።**

### አምስተኛው በሽታ እንዳይዛመት በመከላከል መርዳት የምችለው እንዴት ነው?

- ሲታመሙ በቤት ይቆዩ።
- በተለይም ካስነጠሱ፣ ካሳሉ ወይም አፍንጫ ከጠራረጉ በኋላ፣ እጆችዎን ብዙ ጊዜ ይታጠቡ።
- በሚያስሉበት ወይም በሚያስነጥሱበት ጊዜ አፍንጫዎን እና አፍዎን ይሸፍኑ።
- አይኖችዎን፣ አፍዎን ወይም አፍንጫዎን ከመንካት ይቆጠቡ።
- አምስተኛው በሽታ ካለበት ከማንኛውም ሰው ጋር ኩባያዎችን፣ የመመገቢያ እቃዎችን፣ ምግብን እና መጠጦችን ከመጋራት ይቆጠቡ።
- ህጻናት ወደ አፋቸው የሚከቷቸውን አሻንጉሊቶች እና ሌሎች እቃዎች በሳሙና እና በውሃ በደንብ ያጽዱ።
- የቤት ውስጥ ንጣፎችን ይጥረጉ እንዲሁም ያጽዱ።

---

## ልጄ ከልጅ እንክብካቤ ቀርቶ በቤት መቆየት ይኖርበታል?

**አይ።** ለአምስተኛው በሽታ የተጋለጡ ወይም በምርመራ የተረጋገጡ ልጆች የሚከተሉት ካላጋጠማቸው **በስተቀር** በልጅ እንክብካቤ መገኘት ሊቀጥሉ ይችላሉ፦

- ከሌሎች ምልክቶች ጋር ትኩሳት (100.4°F (38°C) ወይም ከዚያ በላይ የሆነ የሙቀት መጠን) አላቸው።

- በክፍል ውስጥ በሚደረጉ እንቅስቃሴዎች ለመሳተፍ በቂ ደህንነት አይሰማቸውም (ለምሳሌ፦ ከወትሮው የተለየ ድካም፤ ነጭንጭ ወይም ንዝንዝ፤ ወይም ከመደበኛ የበለጠ ማልቀስ)።

**እባክዎ የልጅ እንክብካቤ ፕሮግራምዎን የበሽታ ፖሊሲ ይከተሉ።**

---

### ዋቢዎች

**American Academy of Pediatrics (የአሜሪካ የህጻናት ህክምና አካዳሚ)**

- Caring for our Children, Chapter 3 Health Promotion and Protection, 3.6 Management of Illness, 3.6.1 Inclusion/Exclusion Due to Illness
- Caring for our Children, Chapter 7 Infectious Diseases, 7.3 Respiratory Tract Infections, 7.3.6 Parvovirus B19, 7.3.6.1 Attendance of Children with Erythema Infectiousum (EI) (Parvovirus B19)
- Managing Infectious Diseases in Child Care and Schools, 6th Edition. Pages 107-108

**Centers for Disease Control & Prevention (የበሽታ መቆጣጠሪያ እና መከላከያ ማዕከል)**

- Parvovirus B19 and Fifth Disease. https://www.cdc.gov/parvovirusb19/fifth-disease.html

ይህ ሰነድ ለመጨረሻ ጊዜ የተገመገመው በ Child Care Health Program (የልጅ እንክብካቤ ጤና ፕሮግራም) 7/2023 ነው። - Amharic